በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# የከተሞች ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ክትትል ቢሮ

# የስኬች ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ሞዴል ሰታንዳርድ

በዘርይሁን ተፃፈ

ሰኔ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ይዘቶች


**ምህጻረ-ቃላት** ..... III

**የሰንጠረዥ ዝርዝር** ..... III

**የምስሎች ዝርዝር** ..... IV

**1.መግቢያ** ..... 1

1.1የስታንዳርድ ዝግጅት መነሻ ..... 1

1.2.የስታንዳርዱ ዋና ዓላማ ..... 2

1.2.1. ዝርዝር ዓላማዎች ..... 3

1.3.የተፈፃሚነት ወሰን ..... 3

1.4.የስታንዳርድ ዝግጅት ዘዴዎች ..... 3

1.5.የስታንዳርዱ አስፈላጊነት ..... 4

1.6.የስታንዳርድ ዝግጅት ውስንነት ..... 4

**2. የመሬት አጠቃቀም ምድቦች ስታንዳርድ** ..... 4

2.1. የገጠር የልማት ማዕከላት ጥንስስ ከተሞች የመሬት አጠቃቀም ምድቦች ..... 4

2.1.1. የ ሜሬት አ ጠቃቀምምድቦች ዓይነ ት ..... 4

2.1.2. የ ሜሬት አ ጠቃቀምምድቦች ሜጠን ..... 11

2.1.3. የ ሜሬት አ ጠቃቀምምድቦች ሜጣጣም ..... 11

2.2. የስኬች ፕላን ዋናዋና የመሬት አጠቃቀም ምድቦች መግለጫ ..... 13

2.2.1. መኖሪያ ..... 13

2.2.2. የ ሜኖሪያ አ ካባቢ ግብርና እና የ እረሻ ልማት ..... 14

2.2.3. ገ በያ እና ንግድ ሜዕ ከላት ..... 15

2.2.4. የ ሜህበራዊ አ ገ ልግሎት ተቋማት ..... 16

2.2.5. ሜዝናኛ፣ አ ረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች ..... 27

2.2.6. ለአ ስተዳደር አ ገ ልግሎት ..... 32

2.2.7. የ አ ነ ስተኛ ኢንዱስትሪ ..... 32

**3. የመንገድና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች መረብ ስታንዳርድ ........................................ 36**

3.1. መንገድ ስታንዳርድ .................................................................................................. 36

3.1.1. የመንገድ ሚብቅረጽ .................................................................................................. 36

3.1.2. የመንገድ ስፋት ስታንዳርድ ........................................................................................ 39

3.1.3. የመንገድ ማናኛዎች .................................................................................................. 41

3.1.4. የመንገዶች ተሚራጭዎ ተዳፋትነ ት ማጠን ...................................................................... 41

3.1.5. ብስክሌት እና የእግረኛ መንገድ ሚብ ............................................................................. 42

3.1.6.የ ሚኪና ማቆሚያ ...................................................................................................... 43

3.2.የአገልግሎቶች ስታንዳርድ .......................................................................................... 44

**4. የወረቀት፣ የስኬል እና የብሎክ ስታንዳርዶች ........................................................................ 64**

4.1. የስኬች ፕላን የወረቀት እና ማስፈርት የተማለከተ ........................................................... 64

4.2. የ ብሎክ ማጠን ......................................................................................................... 64

**ማጣቀሻዎች .................................................................................................................. 65**

## ምህጻረ-ቃላት

**CSA - Centeral Statistical Agency**

**FDRE - Federal Democratic Republic of Ethiopia**

**FIIDCA- Federal Integrated Infrastructure Development Coordinating Agency**

**MUDH - Ministry of Urban Development and Housing**

NUPI - National Urban Planing Inistitute

UN - United Nation

**ከ.ል.ቤ.ሚ - ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር**

**ከ.ል.ኮ.ሚ - ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር**

**ማስኤ - የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ**

## የሰንጠረዥ ዝርዝር


ሰንጠረዥ 1.የመሬት አጠቃቀምምድቦች ቀለማት እና ኮዶች ........ 6
ሰንጠረዥ 2. የመሬት አጠቃቀምምድቦች ማጠን ........ 11
ሰንጠረዥ 3. የመሬት አጠቃቀምምድቦች ማጣጣም ........ 12
ሰንጠረዥ 4. በመሬት አጠቃቀምምድቦች የሚከለከሉ ልማቶች ........ 13
ሰንጠረዥ 5. የመኖሪያ አካባቢ የመሬት ሽንሻኖ ስታንዳርድ ........ 14
ሰንጠረዥ 6. የመኖሪያ አካባቢ ግብርና ስታንዳርድ ........ 15
ሰንጠረዥ 7.የገበያ እና የንግድ አይነቶች ........ 16
ሰንጠረዥ 8. የገበያ እና የንግድ ቦታዎች የሽንሻኖ ሽጸንዳርድ ........ 16
ሰንጠረዥ 9. የትምህርት ተቋማት ስታንዳርድ ........ 21
ሰንጠረዥ 10. የጤና ተቋማት ስታንዳርድ ........ 22
ሰንጠረዥ 11. የግብርና ጤና ማዕከላት ስታንዳርድ ........ 23
ሰንጠረዥ12. የአምልኮ እና የቀብር ቦታዎች ስታንዳርድ ........ 24
ሰንጠረዥ 13. የሚጃ ቦታ ስታንዳርድ ........ 25
ሰንጠረዥ 14. የህዝብ መዳጃ ቦታ ስታንዳርድ ........ 26
ሰንጠረዥ 15. የማህበራዊ ደህንነት ስታንዳርድ ........ 27
ሰንጠረዥ 16. የስፖርት ቦታዎች ስታንዳርድ ........ 28
ሰንጠረዥ 17. የአረንጓዴ እና ክፍት ቦታዎች ስታንዳርድ ........ 30

ሰንጠረዥ 18. የአስተዳደር አገልግሎት ቦታዎች ስታንዳርድ ........ 32
ሰንጠረዥ 19. የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ቦታዎች ስታንዳርድ ........ 33
ሰንጠረዥ 20. በሁለት መንገዶች መካከል ያለውስፋት ስታንዳርድ ........ 39
ሰንጠረዥ 21. የመንገዶች ስፋት ስታንዳርድ ........ 40
ሰንጠረዥ 22. መንገዶች ሲገነቡ የማስሞሮች ቁጥር እና ስፋት ስታንዳርድ ........ 40
ሰንጠረዥ 23. የምንገዶች የተዳፋትነት ማጠን ........ 42
ሰንጠረዥ 24. የፓርኪንግ ቦታ ስታንዳርድ ........ 44
ሰንጠረዥ 25. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ8 ሜትር ስፋት ........ 45
ሰንጠረዥ26. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ16.50 ሜስፋት ........ 46
ሰንጠረዥ 27. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ20 ሜትር ........ 47
ሰንጠረዥ 28. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ25 ሜትር ........ 49
ሰንጠረዥ 29. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ30 ሜትር ........ 50
ሰንጠረዥ 30. የመንገድ ቀለማት ስታንዳርድ ........ 51
ሰንጠረዥ 31. የአገልግሎት ቀለማት ስታንዳርድ ........ 53
ሰንጠረዥ 32. የስኬች ፕላን ማስፈርት ስታንዳርድ ........ 64

## የምስሎች ዝርዝር

ምስል 1. ባለ 8 ሜትር መንገድ ........ 45
ምስል 2. ባለ 16.50 ሜትር መንገድ ........ 46
ምስል 3. ባለ 20 ሜትር መንገድ ........ 47
ምስል 4 . ባለ 25 ሜትር መንገድ ........ 48
ምስል 5. ባለ 30 ሜትር መንገድ ........ 49

## 1.መግቢያ

### 1.1የስታንዳርድ ዝግጅት መነሻ

የ2013 ዓ.ም. (እ.አ.አ) የኢትዮጵያ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ አጀንሲ የህዝብ ብዛት ትንበያ መረ ጃ እንደሚያመለክተው በ2009 ዓ.ም. የሀገሪቱ የህዝብ ብዛት ወደ 94,351,001 የደረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 75,265,000 (79.77 በመቶ) የሚሆነው በገጠር ሲኖር ቀሪው 19,086,000 (ወደ 20.23 በመቶ) በከተሞች የሚኖር ነው (CSA,2013)፡፡ በዚሁ መነሻ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ማብቂያ (በ2012) በከተማ የሚኖረው የህዝብ ድርሻ 25 በመቶ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር በሀገራዊ የከተማ ልማት እና የህዝብ አሰፋፈር ፕላን ጥናት እንዳመለከተው የሃገራችን የአከታተም ደረጃ በሶስተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን መጨረሻ ወይም በ2017 ዓ.ም አገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ ስትሰለፍ አሁን ካለንበት (20 በመቶ) ወደ 30 በመቶ፣ በ2022 ዓ.ም ደግሞ 35 በመቶ እና በ2027 ዓ.ም  40 በመቶ ሊደርስ እንደሚችል በ2008 ዓ.ም. ባካሄደው ጥናት አመልክቷል (M.U.D.H., 2016)፡፡

በኢትዮጵያ የከተሞች እድገት እየታየ ያለው በነባር ከተሞች መስፋፋት እና የህዝብ ቁጥር መጨመር ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የገጠር ቀበሌ ማዕከላት በአጭር ጊዜ ውስጥ የህዝብ ቁጥራቸው እየጨመረ እና የኢኮኖሚ፣ ፖሊቲካዊ እና አስተዳደራዊ መዋቅራቸው እያደገ መጥቶ ወደ ከተማነት እየተለወጡ በመሆናቸውም ጭምር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ የሚያሳየው በ2005 ዓ.ም በሀገሪቱ ውስጥ የነበረው የከተሞች ቁጥር 973 የነበረ ቢሆንም (ማስኤ፣ 2005 ዓ.ም) የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ከተማ ፕላን ቢሮ በ2007 ዓ.ም ከክልሎች ያሰባሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው ይኸው አሃዝ ወደ1595 አካባቢ የደረሰ መሆኑን ነው፡፡

የገጠር ማዕከላት ጥንስስ ከተሞች የወደፊት የዕድገት እጣ ፈንታ የተሻለ እና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ለማድረግ ገና ከጅምሩ እያቆጠቆጡ ባሉበት ደረጃ ሥርዓት ይዘው **በስኬች ፕላን** መምራት አስፈላጊነት በከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር የከተማ ፕላን ዝግጅት እና

ትግበራ ስትራቴጂ ውስጥ እንደ አንድ የስትራቴጂ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ በእነዚህ የገጠር ማዕከላት የሚኖረው ህዝብ በአብዛኛው ኑሮው በግብርና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ወደፊት ለእያንዳንዳቸው እንደሚኖራቸው የተነጻጻሪነትና የተወዳዳሪነት እድሎች (comparative and competitive advantage) እየተጠና ካለው ሥርዓተ ከተማ (Urban System) ጋር በተገናዘበ መልኩ ወደ ከተማነት ሲያድጉ ዘርዘር ያለ የመሬት አጠቃቀም የሚያሳይ መሠረታዊ ኘላን እስከሚዘጋጅላቸው ድረስ ዕድገታቸውን በስርዓት ለመምራት የሚያስችል ስኬች ኘላን እንዲዘጋጅላቸው ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ የእስትራቴጂው ሰነድ አመልክቷል፡፡

መሬት ዋናው የሀገራችን ሀብት ምንጭ በመሆኑ የአሁኑ እና መጪው ትውልድም የዚሁ ሀብት ተጠቃሚ መሆን ይገባቸዋል፡፡ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የገጠር የልማት ማዕከላት በፕላን እና በተሟላ የአሰራር ሥርዓት የማይመሩ በመሆናቸዉ በአካባቢያቸዉ ያለዉን ለም የእርሻ መሬት እና በደን የተሸፈነ መሬት በመሻማት ለአካባቢ ሥነ-ምህዳር መዛነፍ ምክንት እየሆኑ በመምጣታቸዉ ይህንን ከወዲሁ በመግታት የአሁኑን ትውልድ በመሬት ሃብት የመጠቀም ፍላጎት ጥያቄ ውስጥ ሳያስገባ ነገር ግን መሬትን በቁጠባ እና እሴት በሚፈጥር መልኩ እየተጠቀሙ የቀጣዩን ትውልድ በዘላቂነት በሀብት የመጠቀም ዋስትና እና ሀገሪቱ ያላትን የተፈጥሮ ሃብት ዘላቂነት ዋስትና በማረጋገጥ የገጠር የልማት ማዕከላትን ከወዲሁ በስርዓት እንዲመሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በየጊዜው እያቆጠቆጡ ለሚመጡ ከተሞች፣ ለገጠር የልማት ማዕከላት እንዲሁም በትላልቅ የልማት ኘሮጀክቶች ምክንያት አዲስ ለሚመሰረቱ ከተሞች የፕላን አዘገጃጀት ሥርዓት ያለመዘርጋቱ፣ ከዚህም አኳያ መታየት ያለባቸው በአገሪቱ በሺህ የሚቆጠሩ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ያሉ ሲሆን እነዚህም ማዕከላት የወደፊት ከተሞች መሰረት ወይም የከተሞች ጥንስስ በመሆናቸው ውስብስብ ሁኔታዎች ከመፈጠራቸው በፊት ከወዲሁ ማዕከላቱን በፕላን መምራት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ከአሠራር ሥርዓት ጋር አያይዞ የፕላን ስትራቴጂያችን ያመለከተ በመሆኑ እና በፌርጅ ስድስት ውስጥ ላሉ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት የፕላን አዘገጃጀት እና አፈፃፀም የሚመራ ስታንዳርድ አለመኖር ለዚህ ሰነድ ዝግጅት መነሻ ሆኗል፡፡

## 1.2.የስታንዳርዱ ዋና ዓላማ

የዚህ ስታንዳርድ ዋና ዓላማ የገጠር የልማት ማዕከላት ጥንስስ ከተሞች የስኬች ፕላን ዝግጅት እና ትግበራን እንዲመራ ነው፡፡

### 1.2.1. ዝርዝር ዓላማዎች

1. በሀገር ደረጃ የስኬች ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ወጥ በሆነ መንገድ እንዲመራ፡፡
2. የስኬች ፕላን ዝግጅት እና ትግበራን ውጤታማ ማድረግ እና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን
3. በገጠር የልማት ማዕከላት ጥንስስ ከተሞች አዋጪ የመሬት አጠቃቀም እንዲኖር ማድረግ
4. በስኬች ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ለሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት በመሬት አጠቃቀም ጉዳዮች ዝቅተኛውን ተፈላጊ የቁራሽ መሬት ስታርድ ማመልከት

## 1.3.የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ስታንዳርድ በኢትዮጵያ በዘጠኙም ክልሎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የስኬች ፕላን ዝግጅትና ትግበራ በሚከናወንባቸው ጥንስስ ከተሞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 1.4.የስታንዳርድ ዝግጅት ዘዴዎች

ይህንን ስታንዳርድ ለማዘጋጀት በሀገር ውስጥና ከሃገር ውጪ የመሬት አጠቃቀም ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ላይ የተዘጋጁ ስታንዳርድ የተመለከቱ ጠቃሚ ተሞክሮ ቅመራ የተከናወነ ሲሆን ለዚሁም ይረዳ ዘንድ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ለተሞክሮ ቅመራና የጥናቱን መረጃዎች ለማሰባሰብ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች የተሰበሰቡት የፁሑፍ መጠይቅ ጥቅም ላይ በማዋል ሲሆን የጥናቱ ናሙናዎች በሀገሪቱ ካሉ ከሥራው ጋር ግኑኝነት ያላቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ እንዲሁም በትግራይ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች ውስጥ ያሉ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው የከተማ ፕላን ተቋማት እና የከተማ ልማት ቢሮዎች የተመረጡ ሲሆን መረጃውን የሞሉት የዘርፍ የሥራ ሂደት ኃላፊዎች እና ባለሞያዎች ናቸው፡፡ የእነዚህም ናሙና ክልሎች ምርጫ ውክልና ባለው ሁኔታ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከጽሁፎችና ሰነዶች ላይ በማተኮር ሲሆን ለዚህም ተግባር ይረዳ ዘንድ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች፣ የስታንዳርድ፣ የማዋል ሰነዶች፣ መፃህፍት፣ የከተማ ልማት ፖሊሲና ስትራተጂ ደኩመንቶች እና ከኢንተርኔት የሚገኙ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 1.5.የስታንዳርዱ አስፈላጊነት

ይህ ስታንዳርድ ለስኬች ፕላን አዘጋጆች፣ ተግባሪዎች፣ በየደረጃው ላሉ ውሳኔ ሰጪዎች፣ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ሂደት በዕለት ተዕለት የፕላን ሥራቸው መሪ ሆኖ የሚጠቀሙበት ከመሆኑም በላይ ሰነዱ በሀገራችን በገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ላይ ጥናት ለሚያካሂዱ ተጨማሪ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

### 1.6.የስታንዳርድ ዝግጅት ውስንነት

ለዚህ ስታንዳርድ ዝግጅት ከሌሎች አገሮች የሚደረጉ የተሞከሮ ቅመራዎች የተከናወኑት ከኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በተገኙ መረጃዎች ብቻ መሆኑ የጥናቱ ውስንነት ነው፡፡

# 2. የመሬት አጠቃቀም ምድቦች ስታንዳርድ

## 2.1. የገጠር የልማት ማዕከላት ጥንስስ ከተሞች የመሬት አጠቃቀም ምድቦች

### 2.1.1. የ ሜሬት አ ጠቃቀምምድቦች ዓይነ ት

በገጠፈር የልማት ማዕከላት በስኬች ፕላን ዝግጅት የሚካተቱ የመሬት አጠቃቀም ምድቦች በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመኖሪያ
2. የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት
3. ገበያ እና ንግድ ማዕከላት
4. የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት

5. መዝናኛ፣ አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች

6. ለአስተዳደር አገልግሎት

7. የመንገድ እና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች

8. የአነስተኛ ኢንዱስትሪ

በገጠር የልማት ማዕከላት ጥንስስ ከተሞች የስኬች ፕላን ዝግጅት ያሉ የመሬት አጠቃቀም ምድቦች በሚከተሉት የቀለማት ዝርዝር መዘጋጀት አለባቸው

## ሰንጠረዥ1.የ ሜሬት አጠቃቀምምድቦች ቀለማት እና ኮዶች

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ድልድል | ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች | መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፊደላት(Letter) | ቀለማት(Color) | ጥቁር እና ነጭ |
| | | | | | |
| 1 | መኖሪያ | ነባር የመኖሪያ ቤት | R-1 | ቢጫ | Horizontal hatch |
| | | የወደፊቱ የመኖሪያ ቤት ቦታ | R-2 | | |
| | | ከፍተኛ ጥግግት ያለበት ቦታ | R-3 | | |
| | | ልዩ ቤቶች(Special housing) | R-4 | | |
| | | | | | |
| 2 | ለገበያ እና ንግድ ተቋማት | ሱቆች | CBA-1 | ቀይ | Normal Square Hatch |
| | | ምግብ ቤቶች፣መጠጥ ቤቶች | CBA-2 | | |
| | | አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | CBA-3 | | |
| | | የንግድ ማዕከላት | CBA-4 | | |
| | | ገበያ | CBA-5 | | |
| | | | | | |

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ድልድል | ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች | መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፊደላት(Letter) | ቀለማት(Color) | ጥቁር እና ነጭ |
| 3 | **የማህበራዊ አገልግሎት** | **ትምህርት** | S-1 | ሰማያዊ | 45° Hatch |
| | | መዋዕለ ህፃናት | S-11 | | |
| | | አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | S-12 | | |
| | | ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | S-13 | | |
| | | **ጤና** | S-2 | | |
| | | ጤና ኬላ | S-21 | | |
| | | ጤና ጣቢያ | S-22 | | |
| | | **የህዝብ መገልገያ** (Community and cultural facilities) | S-3 | | |
| | | የህፃናት እና የወጣቶች ማዕከል | S-34 | | |
| | | ማረጃ ቦታ | S-42 | | |
| | | የህዝብ መፀዳጃ | S-43 | | |
| | | የማህበራዊ ደህንነት(እድር..) | S-44 | | |
| | | ለተለየ አገልግሎት የሚውሉ | S-5 | | |

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ድልድል | ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች | መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፊደላት(Letter) | ቀለማት(Color) | ጥቁር እና ነጭ |
| | | (Special functions) | | | |
| | | የታሪክ እና ቅርሳቅርስ ማዕከላት | S-52 | | |
| | | | | | |
| 4 | የመዝናኛ፣ አረንጓዴ እና ክፍት ቦታዎች | ክፍት ቦታዎች | EA-1 | አረንጓዴ | Square dotted |
| | | ስፖርት ሜዳዎች | EA — 83 | | |
| | | የአረንጓዴ መዝናኛ ቦታዎች | EA - 65 | | |
| | | አምልኮና የቀብር ቦታዎች | EA - 68 | | |
| | | የህፃናት መጫወቻ ቦታ | EA - 63 | | |
| 5. | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | EA - 2 | አረንጓዴ | Square |
| 6 | **አስተዳደራዊ ተቋማት** | መንግስታዊ ተቋማት | AD-1 | ቡናአይነት | |
| | | መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት | AD-2 | | |

| **ተ.ቁ** | **የመሬት አጠቃቀም ድልድል** | **ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች** | **መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding)** | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | **ፊደላት(Letter)** | **ቀለማት(Color)** | **ጥቁር እና ነጭ** |
| | | ንኡስ ፖሊስ ጣቢያ | AD-3 | | |
| | | የማህበራዊ ፍርድቤት | AD-6 | | |
| 7. | **የአነስተኛ ኢንዱስትሪ** | **ኢንዱስትሪ** | P-1 | ወይንጠጅ | አግድም የተሰመረበት ሳጥን |
| | | አነስተኛ ኢንዱስትሪ | P-3 | | |
| 8. | **መንገድ** | Road | RTU-1 | ግራጫ | ________ |

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ድልድል | ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች | መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፊደላት(Letter) | ቀለማት(Color) | ጥቁር እና ነጭ |
| | | ዋና መንገድ | RTU-(PA) | | ............ ............ ______ |
| | | የዋና መንገድ መጋቢ | RTU-(SA) | | |
| | | መጋቢ | RTU-(C) | | |
| | | የዉስጥ ለዉስጥ መንገድ | RTU-(L) | | |
| 9. | የመሠረተልማት እና ሌሎች አገልግሎቶች | የህዝብ ማመላለሻ መናኸሪያ | RTU-24 | | |
| | | የቧምቧ መሥመር | RTU-3 | | |
| | | የኤሌክትሪክ መሥመር | RTU-4 | | |
| | | የሥልክ መሥመር | RTU-5 | | |

### 2.1.2. የ ሜ ት አ ጠቃቀ ምምድቦ ች ማጠን

## ሰ ን ጠረ ዥ 2. የ ሜ ት አ ጠቃቀ ምምድቦ ች ማጠን

| No. | ድልድሎች | መነሻ ድልድል በመቶኛ |
|---|---|---|
| 1 | የመኖሪያ | 20-25 |
| 2 | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | 10-20 |
| 3 | ገበያ እና ንግድ ማዕከላት | 3-7 |
| 4 | የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት | 10-20 |
| 5 | መዝናኛ፣ አረንጓዴ እና ክፍት ቦታዎች | 15-25 |
| 6 | ለአስተዳደር አገልግሎት | 2-5 |
| 7 | የመንገድ እና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች | 15-30 |
| 8 | የአነስተኛ ኢንዱስትሪ | 5-10 |

ምንጭ፡ ከልቤሚ፣ 2009

### 2.1.3. የ ሜ ት አ ጠቃቀ ምምድቦ ች ማጣጣም

በስኬች ፕላን ዝግጅት ወቅት የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም ምድቦች ለሚቀጥሉት የፕላን ዘመን ፕላን ሲሰራ ኩታ ገጠም የሆኑ የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች በፕላን ዝግጅት ወቅት እርስ በርስ የሚጣጣሙ መሆናቸው መለዬት አለበት፡፡

በመሆኑም የሚቀጥለው ሰንጠረዥ በስኬች ፕላን ዝግጅት ወቅት የሚጣጣሙና የማይጣጣሙ ድልድሎችን ያሳያል፡፡

## ሰንጠረዥ 3. የሜሬት አጠቃቀምምድቦች ማጣጣም

| ተ.ቁ | ዓነ ቶች | የመኖሪያ | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | ገበያ እና ንግድ ማዕከላት | የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት | መዝናኛ፣ አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች | ለአስተዳደር አገልግሎት | የመንገድ እና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች | የአነስተኛ ኢንዱስትሪ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመኖሪያ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | X |
| 2 | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | | | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | |
| 3 | ገበያ እና ንግድ ማዕከላት | X | ✓ | | X | X | X | | ✓ |
| 4 | የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት | ✓ | ✓ | X | | X | ✓ | | X |
| 5 | መዝናኛ፣ አረንጓዴ እና ክፍት ቦታዎች | ✓ | ✓ | X | X | | X | | X |
| 6 | ለአስተዳደር አገልግሎት | ✓ | ✓ | X | ✓ | ✓ | | | X |
| 7 | የመንገድ እና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች | | | | | | | | |
| 8 | የአነስተኛ ኢንዱስትሪ | X | X | ✓ | X | X | X | X | |

✓ - ይጣጣማል X- አይጣጣምም

## ሰንጠረዥ4. በሜሬት አጠቃቀምምድቦች የ ሚከለከሉ ልማቶች

| No. | ድልድሎች | በዚህ ምድብ የተከለከሉ ልማቶች |
|---|---|---|
| 1 | የመኖሪያ | ኢነዱስትሪ፣ ወታደራዊ ተቋማት፣ ቆሻሻ መጣያ፣ የቀብር ስፍራ፣ |
| 2 | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | ኢነዱስትሪ፣ ወታደራዊ ተቋማት፣ ቆሻሻ መጣያ፣ የቀብር ስፍራ |
| 3 | ገበያ እና ንግድ ማዕከላት | ቆሻሻ መጣያ፣ የቀብር ስፍራ |
| 4 | የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት | ኢነዱስትሪ፣ ቆሻሻ መጣያ፣ መዝናኛ፣ ገበያ |
| 5 | መዝናኛ፣ አረንጓዴ እና ክፍት ቦታዎች | ኢነዱስትሪ፣ ቆሻሻ መጣያ፣ የቀብር ስፍራ |
| 6 | ለአስተዳደር አገልግሎት | ኢነዱስትሪ፣ ቆሻሻ መጣያ፣ የቀብር ስፍራ |
| 7 | የመንገድ እና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች | |
| 8 | የአነስተኛ ኢንዱስትሪ | ቆሻሻ መጣያ፣ የቀብር ስፍራ |

## 2.2. የስኬች ፕላን ዋናዋና የመሬት አጠቃቀም ምድቦች መግለጫ

### 2.2.1. መኖሪያ

**የመኖሪያ አካባቢ የሳይት ምርጫ**

- ጥቁር መረሬ አፈር በሚገኙባቸው አካባቢዎች ባይሆኑ ይመረጣል
- የመሬት እጥረት ካላጋጠመ በስተቀር የመኖሪያ ሰፈሮች በማዕከሉ በሁሉም አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፡፡
- መጠነኛ ተዳፋትነት ባሉባቸው አካባቢዎች እንዲሆኑ ማድረግ፤ የተዳፋትነት መጠናቸው ከ2% - 15% ሊመረጥ የሚችል ቢሆንም ከ2% - 8% ቢሆን ግን በጣም ይመከራል
- የተፈጥሮ አደጋዎች ከሚፈጠሩባቸው አካባቢዎች በጣም የራቁ መሆን አለባቸው ለምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የመሬት መንሸራተት፣ የተፈጥሮ በሽታዎች፣ ወረርሽኞች እና የመሳሰሉት፡፡

## የ ቁራሽ ሜት ስታንዳርድ

የመኖሪያ አካባቢ የቁራሽ መሬት ሽንሻኖ የመሰረተ ልማት ወጪን ለመቀነስ አራት ማእዘን ቢሆን የሚመረጥ ሲሆን  በፊት ለፊት በመንገድ በኩል ያለው ስፋት በጎን በኩል ካለው የሚያንስ መሆን አለበት፡፡ ብዙ ጊዜ ግን የፊት ለፊቱ ስፋት ከጎን ስፋት በሁለት እጥፍ ያነሰ ነው፡፡ ማንኛውም የመኖሪያ የቁራሽ መሬት ሽንሻኖ ወደ መንገድ የሚያስወጣው የመንገድ መስመር ሊኖረው ይገባል፡፡

### ሰንጠረዥ5. የ መኖሪያ አካባቢ የ ሜት ሽንሻኖ ስታንዳርድ

| | የመሬት አጠቃቀም ምድብ | የ ቁራሽ ሜት  መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | በዝቅተኛ ጥግግት | በከፍተኛ ጥግግት |
| 1 | የግል መኖሪያ | 500 -1000 ካሜ | 200 - 300 ካሜ |

**የዝቅተኛ እና የከፍተኛ ጥግግት መግለጫ**

በገጠር የልማት ማዕከል ጥንስስ ከተማ የፕላን ወሰን ውስጥ በአማካይ በአንድ ካሬ ኪሎሜትር ውስጥ ሊኖር የሚገባው የቤቶች ቁጥር እነደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያ የሚችል ሲሆን በዚህ ስታንዳርድ ከፍተኛ ጥግግት የሚባለው በአንድ ካሬ ኪሎሜትር ውስጥ ከ1000 ቤት በላይ ይኖራል ተብሎ ሲገመት ሲሆን ዝቅተኛ ጥግግት የሚባለው በአንድ ካሬ ኪሎሜትር ውስጥ ከ400 ቤት በታች ይኖራል ተብሎ ሲገመት ነው፡፡

### 2.2.2. የ መኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የ እረሻ ልማት

የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት የመሬት አጠቃቀም ምድብ በገጠር ማዕከላት ውስጥ ቀደም ሲል አርሶ አደሩ በያዘው ቁራሽ መሬት ላይ ማንኛውንም ዓይነት ቤት ሰርቶ የተለያዩ የግብርና ዓይነቶችን የኑሮ መሠረት አድርጎ የሚኖርበት ቦታ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የመሬት ምድብ በገጠር ማዕከሉ የፕላን ወሰን ውስጥ ከማዕከል ወጣ ባለ አካባቢ እና ከዋናው መንገድ ውጭ በሌሎች በሁሉም ስፍራዎች ሊገኝ የሚችል ነው፡፡ ይህም የመሬት አጠቃቀም ነባራዊውን የመሬት አጠቃቀም ሳይለውጥ የሚታቀድ ነው፡፡

የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት የመሬት ምድብ በሂደት በሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዓይነቶች እስኪተካ እና የገጠር ማዕከሏ በሂደት ወደከተማነት እስክትለወጥ ድረስ አብዛኛውን ቦታ ይዞ መቆዬቱ አይቀርም፡፡

**የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት የሳይት ምርጫ**

- የእርሻ ሥፍራዎች ውሃማ አካባቢዎች እንዲሆኑ ይመከራል
- የእንስሳ እርባታ ቦታዎች በነፋስ አቅጣጫ ላይ መሆን የለባቸውም
- የግብርና ሥፍራዎች የተዳፋትነት መጠናቸው ከ1-10% በሆኑ አካባቢዎች ቢሆን ይመረጣል

### ሰንጠረዥ 6. የመኖሪያ አካባቢ ግብርና ስታንዳርድ

| የመኖሪያ አካባቢ ግብርና | አስፈላጊው የመሬት ስፋት ተመጣጣኝነት |
|---|---|
| የከብት እርባታ | 1 ከብት፡ 50 ካሜ |
| የከብቶች ማደለቢያ | 1 ከብት፡50 ካሜ |
| የአሳማ እርባታ | 1 ከብት፡75 ካሜ |
| የፍየልና በጎች እርባታ | 1 ፍየል ወይ በግ ፡14 ካሜ |
| የዶሮ እርባታ | 12ዶሮ፡ 1ካሜ |
| የንብ ማነቢያ | 100- 200 ካሜ |

ምንጭ፡ ከልኮሚ፣ 2005

### 2.2.3. ገበያ እና ንግድ ማዕከላት

**ገበያ እና ንግድ ማዕከላት ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

የንግድ አካባቢዎች በሚከተሉት አካባቢዎች እንዲሆኑ ይመከራል

- በገጠር ማዕከሏ ማዕከል እና በማዕከል አቅራቢያ
- በዋናዋና መንገዶች ዳርቻ

- በዋናዋና መንገዶች መጋጠሚያ

## ሰንጠረዥ7.የገበያ እና የንግድ አይነቶች

የገበያ እና ንግድ ማዕከላት የመሬት አጠቃቀም የተለያዩ የንግድ ዓይነቶችን ያቀፈ ነው::

| የልማቱ ዓይነት | ትርጉም |
|---|---|
| ገበያ | በክፍት የገበያ ቦታዎች ከእንሰሳ ውጭ የመገበያያ ቦታ ነው |
| የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ | በአንድ ክፍል ዉስጥ የተለያዩ የፍጆታ ሸቀጦች የሚሸጥበት ቦታ |
| የመጠጥ እና ምግብ ቤቶች | ምግብ እና መጠጥ የሚሸጥበት ቤት |
| የእንስሳ ገበያ | ማንኛውም እንስሳ የሚሸጥበት ቦታ |
| መጋዘን | የእህል በረንዳን ጨምሮ የሁሉም አዝርዕት ማከማቻ |
| የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | የፋይናንስ ተቋማት |
| ፋርማሲ | የመድሃኒት መሸጫ |

## ሰንጠረዥ8. የገበያ እና የንግድ ቦታዎች የሽንሻኖ ሽጻንዳርድ

| የልማቱ ዓይነት | የቁራሽ መሬት ስፋት | መደዳ ቤት በንግድ ሰፈር |
|---|---|---|
| ገበያ | 2 - 7 ሄክታር | |
| የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ | 100 - 300 ካ.ሜ | 50 — 75 ካ.ሜ |
| የመጠጥ እና ምግብ ቤቶች | 1000 - 3000 ካ.ሜ | 300-500 ካ.ሜ |
| የእንስሳ ገበያ | 0.5 - 1.3 ሄክታር | |
| ፍዬልና በግ | ለአንድ እንስሳ 4 ካ.ሜ | |
| ለጋማ ከብት | ለአንድ እንስሳ 6 ካ.ሜ | |
| መጋዘን | 500 - 2500 ካ.ሜ ወይም በኩንታል 0.5 ካ.ሜ | |
| የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | 500 - 1000 ካ.ሜ | |

### 2.2.4. የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት

**ሀ. የትምህርት ተቋማት**

**የትምህርት ተቋማት ተስማሚ የሳይት ምርጫ (በጥቅል)**

- የትምህርት ተቋማት የመንገድ መስመሮች ባሉባቸው አካባቢዎች መሆን አለባቸው
- በጣም ከተጨናነቀ የመንገድ ትራፊክ መራቅ አለባቸው
- ለመኖሪያ ሰፈሮች የቀረቡ መሆን አለባቸው
- የተዳፋትነት መጠናቸው ዝቅተኛ ሆኖ ከ2-10% ቢሆን ይመከራል
- የተፈጥሮ አደጋዎች አና ወረርሽኞች ከሚከሰቱባቸው አካባቢዎ የራቁ መሆን አለባቸው
- ከድምፅ በካይ ተቋማት እና ከንግድ ማዕከላት ለምሳሌ ከአነስተኛ ኢንዱስትሪ፣ ከሆቴሎች፣ ከጠጅ ቤቶች እና ከመሳሰሉት የራቁ መሆን አለባቸው፡፡

**ዝርዝር ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

I. **የቅድመ - መደበኛ ትምህርት**

- አካባቢው የፀዳና ለሕፃናት ተስማሚ የሆነ ንጹህ አየር ያለው፣ ከቆሻሻ መጣያ፣ ከፍሳሽ፣ ከወንዞች፣ ከኩሬዎች፣ ከረግረግና ከገደል የራቀና ሕፃናትን የሚተናኮሉ አውሬዎችና ነፍሳት የሌሉበት፤
- ለትራፊክ አደጋ የማያጋልጥ፤
- በቀላሉ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚገኝበት፤
- ከመንገድ ዳር ገባ ያለ፤
- ከመጠጥ ቤቶች የራቀ፤
- ቢቻል በአቅራቢያው ሆስፒታል፤ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ያለው ሆኖ ተላላፊ በሽታ ከሚከላከሉ እንደ ሳንባ ነቀርሳ መከላኪያና ከመሳሰሉት የጤና ድርጅቶች አቅራቢያ ባይሆን የተሻለ ነው፡፡
- ፀጥታ የሰፈነበት አካባቢ፤ የእንጨት መሰንጠቂያ፤ ወፍጮ ቤት፣ ሙዚቃ ቤት … ወዘተ ከመሳሰሉት የራቀ፤
- ሰፊ ቦታና በቂ የመጫወቻ ሥፍራ ያለው፤

- ለሕፃናቱ እንዳይርቅ ከቤታቸው በአማካይ ከአንድ ኪሎ ሜትር ያልራቀ ቦታ ሊመረጥለት ይገባል፡፡
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ሕንፃዎች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት ከስሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላና ወዘተ ማቴሪያሎች ሊሠሩ ይችላሉ፡፡

**የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት መጠን**

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት በአንድ ክፍል ውስጥ ከ40 ሕፃናት በላይ ማስተናገድ የለበትም፡፡ አንድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም እያንዳንዳቸው 7x9=63 ካ.ሜ የሆኑ እስከ 6 ክፍሎች ይችላል፡፡ በእነዚህም ክፍሎች ውስጥ 6 x 40=240 ሕፃናት ሊያስተናግድ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት ከ1200 እስከ 1500 ካ.ሜ. የቁራሽ መሬት ይፈላጋሉ፡፡

**II. የመጀመሪ ደረጃ ት/ቤት**

**አነደኛ ደረጃ የመጀመሪያሳይክል (1-4) የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች**

ተማሪዎች ከመኖሪያ ክልላቸው በቅርብ ርቀት ላይ ተመላልሰው መማር የሚችሉበት ሆኖ ት/ቤቱ የመማር ማስተማር ተግባር ከሚያደናቅፉ ሁኔታዎች ማለትም ከዋና መንገድ፣ ከአዋኪ ድምፅና ጫጫታ፣ ከመጥፎ ጠረን፣ ከመጠጥ ቤት፣ ከከፍተኛ ትራፊክ ፍሰት፣ ከወንዞችና ገደላማ ቦታዎች፣ ከገበያና ከፋብሪካ እንዲሁም የተማሪውን ስነምግባር ከሚያበላሹ ከቪዲዮ ቤቶችና ተለጣፊ ሱቆች ከመሣሰሉት የራቀ መሆን ይኖርበታል፡፡

**የት/ቤት መጠን**

የአንድ ት/ቤት መጠን በመማሪያ ክፍሎችና በሚኖሩት የተማሪዎች ብዛት የሚወሰን ሲሆን የመማሪያ ክፍሎች ብዛት ደግሞ በተማሪ ቁጥር ይወሰናል፡፡

የልዩ ፍላጐት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ከሌሎች በተለየ ክህሎትንና ትምህርትን ለመስጠት የሚያስችሉ ሌሎች ተጨማሪ መማሪያ ክፍሎችና ተስማሚ የሆኑ የትምህርት መሣሪያዎች ማሟላት ይገባል፡፡

## የክፍል መጠን አደረጃጀት

አንድ ት/ቤት ለመጀመሪያ ደረጃ ለመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ቢያንስ አራት የመማሪያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፡፡ እንዲሁም ለሁለቱም ሣይክሎች /1-8/ ቢያንስ ስምንት የመማሪያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

## የምድረግቢ ሥፋት

- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት(ከ1-8) ቤት እንደ መማሪያ ክፍሎች ብዛት ከ15,000 እስከ 25,000 ካሬ ሜትር የሚሆን የቦታ ስፋት ይኖረዋል፡፡
- በገጠር ት/ቤቶች ግን ት/ቤቶች ሰፊ ቦታ እንዲኖራቸው ማድረጉ የት/ቤቶች የውስጥ ገቢ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል ከላይ የተጠቀሰው የቦታ መጠን እንዳለ ሥራ ላይ ይውላል።
- ለትምህርቱ ጥራት መጠበቅ ሲባል አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ከ2000 ተማሪዎች በላይ ማስተናገድ የለበትም።
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍል ስፋት ከ50 እስከ 56 ካሬ ሜትር ይሆናል፡፡

ይህም ለት/ቤት ህንፃ፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ የጓሮ አትክልት ቦታና ለተማሪዎች የእረፍት ሰዓት መዝናኛና መጫወቻ እንደዚሁም ቀደም ሲል በተገለፀው የክፍል መጠን አደረጃጀት መሠረት ት/ቤቱን ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች እንዲኖሩት ያስችላል፡፡

## III. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አደረጃጀት

በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል ተከፍሎ የሚሰጥ ሲሆን በመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ከ9ኛ- 10ኛ ክፍል በሁለተኛ ሳይክል ደግሞ ከ11ኛ–12ኛ ክፍል የሚሰጥ ነው፡፡

የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች

ጥራት ያለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለማስፋፋት ት/ቤቶቹ ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ ት/ቤት የሚከተሉትን መሰፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

- ተማሪዎች ተመላልሰው ሊማሩ የሚችሉበት ሆኖ ከተማሪዎች መኖሪያ ክልል አማካይ ርቀት ከ3–5 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፣ /እንደየ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል
- የመኪና መንገድ፣ መገናኛ ያለው ወይንም ከመገናኛ መንገድ ቅርበት ያለው፣
- የአካባቢውን ጸጥታ ከሚያውኩ ከትራፊክ መጨናነቅ፣ ከመጠጥ ቤቶች፣ ከገበያ ፣ከወንዝ፣ ከጫት መቃሚያ ቤቶች፣ ከሙዚቃ ቤቶች የራቀ፣
- የት/ቤቱ ግቢ ወጣ ገባ ያልበዛበት ወይም ሜዳማ የሆነ ቦታ ያለው፣
- ለትምህርት ኘሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆን በቂና ተስማሚ የእስፖርትና የጓሮ አትክልት ቦታ ያለው፣
- የመሬቱ አቀማመጥ ለጎርፍ ፣ ለፍሳሽ ለከባድ ንፋስና ለአቧራ ያልተጋለጠ፣
- የውኃ የመብራትና ስልክ አገልግሎት ያለው፣

የምድረ ግቢው ገጽታ አደረጃጀት

የሚቋቋሙ ት/ቤቶች በተማሪዎች የመማርና የማስተማር ውጤቶች ላይ ተፅዕኖ ከሚያስከተሉ ነገሮች ነፃ መሆን አለባቸው፡፡ አንድ ት/ቤት የሚከተሉት ገጽታና አደረጃጀት ይኖሩታል፡፡

- ለመማሪያና ለተለያዩ አገልግልቶች የሚውሉ ብሎኮችና ክፍሎች እንደ ሥራ ቅርበታቸውና አገልግሎታቸው የተሰሩ፣
- የህንፃዎች አደረጃጀት የምድረ ግቢውን ውበት አጠባበቅ ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ የመኪና ማቆሚያና የእግር መንገዶች እንደ አስፈላጊነቱ የተሠራለት ፣
- የመዝናኛ መጫዎቻ ቦታዎች / ሜዳዎች/ ያሉት
- በአጥር የተከለለና የተከበረ፣
- ከክፍል ውጭ ለሚሰጡ ትምህርቶች /እርሻ ፣ እስፖርት . . ./ ተመጣጣኝ ቦታ በግቢው ውስጥ ያሉት ፣

- በአጠቃላይ የህንፃዎች አደረጃጀትና የመንገዶች አቀማመጥ ለትምህርት አሰጣጥ አመቺና መስኅብ ያለው ይሆናሉ፡፡

**የምድረ ግቢው ስፋት**

አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሊኖረው የሚገባው የምድረ ግቢው ስፋትና መጠን እንደተማሪዎች የዕድገት ደረጃና የእንቅስቃሴ ሁኔታ የተለያዩ ትምህርት ኘሮግራሞች ሊያቅፍ ስለሚችል ከ30,000 – 60,000 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ቦታ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም በከተማና በገጠር እንደየሁኔታው ሊለያይ የሚችል ሲሆን በገጠር የትምህርት ቤቶችን የውስጥ ገቢ ለማጠናከር እንዲቻል የተቀመጠው አሐዝ ባለበት የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ነገር ግን በከተማ ካለው የቦታ ጥበት አኳያ የት/ቤቶች ህንፃዎች ፎቆች ሊሆኑ እንደሚችሉ እና እንዲሁም የእስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ከአንድ አገልግሎት በላይ እንዲሰጡ ተደርገው ይሠራሉ፡፡

## ሰንጠረዥ9. የትምህርት ተቋማት ስታንዳርድ

| **የትምህርት ተቋማት** | **ለአንዱ ተቋም አስፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት** |
|---|---|
| መዋዕለ ህጻናት | ከ1200 - 1500 ካሜ |
| **የመጀመሪ ደረጃ ት/ቤት**<br><br>አንደኛ ሳይክል (1-4) | 5000 - 10000 ካሜ |
| የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት(1-8) | 15000-25000 ካሜ |
| ሁለተኛ ደረጃ (9-12) | 30000- 60000 ካሜ |

**ለ. የጤና ተቋማት**

**የጤና ተቋማት ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

- የጤና ተቋማት በእግር በቀላል ሊደረስ በሚቻልበት ቦታ ላይ በመኖሪያ አካባቢ ወይም በማዕከል እና መኖሪያ አካባቢ በሚገኙ መንገዶች መገናኛ አጠገብ መሆን አለባቸው
- በዋና መንገዶች ዳርቻዎች ላይ መሆን አለባቸው
- የጤና ማዕከላት የድምጽ ብክለት በሌሌበት ቦታ መሆን አለባቸው

**ሰንጠረዥ- 10 የጤና ተቋማት ስታንዳርድ**

## ሰንጠረዥ10. የ ጤና ተቋማት ስ ታንዳርድ

| የጤና ተቋማት | ተቋማት ሰፈላጊው የወለል ስፋት | አሰፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት | የጤና ተቋማት እና የህዝብ ብዛት ተመጣጣኝነት |
|---|---|---|---|
| ጤና ጣቢያ | 840 ካሜ | 5000 ካሜ | 1:15000 -1:25000 |
| ክሊኒክ | ------- | 1000 - 2000 ካሜ | |
| ፋርማሲ | | 100 ካ.ሜ - 300 ካ.ሜ | |
| የጤና ኬላ 1ኛ ትውልድ | 50 ካሜ | 500 ካሜ | 1:3000- 1:5000 |
| የጤና ኬላ 2ኛ ትውልድ | 300 ካሜ | 3000 ካሜ | |

**የግብርና ጤና ማዕከላት**

**የግብርና ጤና ማዕከላት ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

- የግብርና ጤና ማዕከላት በማዕከሉ ዳርቻ አካባቢ ሆኖ ከ10% በላይ የተዳፋትነት መጠን ባለው ቦታ ላይ ሆኖ የገጠር ማዕከሉን የመጠጥ ውሃ ብክለት መከላከል በሚቻልበት ሁኔታ በዝቅተኛ ቦታ ላይ መሆን አለበት

**ሰንጠረዥ-11 የግብርና ጤና ማዕከላት ስታንዳርድ**

## ሰንጠረዥ 11. የግብርና ጤና ማዕከላት ስታንዳርድ

| የግብርና ጤና ማዕከላት | ተቋማት ሰፈላጊው የወለል ስፋት | አሰፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት |
|---|---|---|
| የከብቶች ህክምና ማዕከል | 200 ካሜ | 0.5 — 1 ሄክታር |

**ሐ. የአምልኮ እና ቀብር ቦታዎች**

**የአምልኮ እና ቀብር ቦታዎች ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

የአምልኮ ቦታዎች ቤተክርስትያንን፣ መስኪድን፣ እና ሌሎች የማምለኪያ ቦታዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን የእነዚህ ቦታዎች ተፈላጊውን የመሬት ስፋት መጠን መገመት አሰቸጋሪ በመሆኑ ባጠቃላይ ግን ከቆይታ በኋላ የተለያዩ የማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ በመሆናቸው እና በቂ የፓርኪንግ አገልግሎት የሚፈልጉ እንደመሆናቸው መጠን ከከተማው ክልል ዳርቻ አካባቢ ሰፋ ያለ ቦታ ይዘው የሚለሙ ናቸው፡፡

ለነዚህ ለተለያዩ የማምለኪያ ቦታዎች የቦታ ስፋት እና አቅጣጫ ለመወሰን የሚታዩ ነጥቦች

- የእምነቱ ተከታይ የህዝብ ብዛት
- ከመኖሪያ አካባቢ በእገር ተደራሽ መሆኑ

**የአምልኮ ቦታዎች ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

- ለዋና መንገዶች የቀረቡ መሆን አለባቸው

- በቦታ ላይ ያለው ስርጭት ከእምነቱ ተከታይ ህዝብ ቁጥር አንፃር ተመጣጣኝ ሆኖ በተመሳሳይ ሃይማኖት እና በተመሳሳይ ዶክትሪን የማለኪያ ቦታዎች ድግግሞሽ ከአንድ ኪ.ሜ. በላይ በሚደርስ ልዩነት እንዲኖር ቢደረግ መልካም ነው
- ለትምህርት እና ጤና ተቋማት የቀረቡ መሆን የለባቸውም

**የዘላቂ ማረፊያ ሥፍራዎችን ለመወሰን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማየት:-**

- በገጠር ማዕከሉ የፕላን ወሰን ዳርቻ ወጣ ባለ ቦታ ሆኖ በዘላቂ ማረፊያ እና በሌሎች ልማቶች መካከል ልዩነት የሚያሳይ የዳርቻ አካባቢ መኖር አለበት
- ከጤና፣ ከትምህርት እና ከመዝናኛ ሥፍራዎች በተቃራኒው የራቀ መሆን አለበት
- ሥፍራው መንገድ ሊኖረው ይገባል;
- የተዳፋትነት መጠኑ ከ10% በታች ቢሆን ይመረጣል
- ዉሃ በማያሰርጉ እና ጠንካራ የአፈር አይነት ባለበት ቦታ መሆን አለበት
- የቦታው ስፋት እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በየዕምነት ተከታዩ ብዛት እና ባለው የሞት መጠን ይወሰናል

**ሰንጠረዥ- 12 የአምልኮ እና የቀብር ቦታዎች ስታንዳርድ**

## ሰንጠረዥ12. የአምልኮ እና የቀብር ቦታዎች ስታንዳርድ

| የአምልኮ እና ቀብር ቦታዎች | ስፈላጊው የወለል ስፋት | አስፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት |
|---|---|---|
| የአምልኮ ቦታዎች | 400 - 1000ካሜ | 0.5 - 3 ሄክታር |
| ቀብር ቦታዎች | ------------ | 1 ሄክታር |

**መ. የህዝብ መገልገያ ቦታዎች**

**1. ማረጃ ቦታ**

**የእርድ ሥፍራዎችን ለመወሰን የሚከተሉትን መሥፈርቶች ማየት ያስፈልጋል**

- በአየር ከሚመጡ በካይ ከሆኑ ተቋማት መራቅ አለበት(ጭስ፣ አመድ፣ አቧራ፣ ሽታ ካላቸው ቦታዎች…)

- ለመኖሪያ፣ ለት/ቤቶች፣ ለማምለኪያ ስፍራዎች ..ወዘተ የቀረበ መሆን የለበትም
- የእርድ ሥፍራዎች በአውሮፕላን የበረራ መስመር ላይ መሆን የለባቸውም
- የእርድ ሥፍራዎች በከተማው ዳርቻ አካባቢ መሆን አለበት
- ለሥራው በቂ ቦታ ያለው መሆን
- የእርድ ሥፍራዎች የተዳፋትነት መጠን ከ5% በላይ መሆን አለባቸው
- ከውሃ ተፋሰስ መስመሮች የራቀ መሆን አለበት
- በንፋስ አቅጣጫ መሆን የለበትም
- የወደፊት የማስፋፊያ ቦታ ላይ መሆን የለበትም
- የማረጃ ቦታዎች በጥሩ አጥር መከለል አለባቸው

**የማረጃ ቦታ ስታንዳርድ**

**በገጠር ማዕከላት በገበያ ቀናት እና በበዓላት ቀናት የሚታረደው የከብት ብዛት ታሳቢ በማድረግ ለማረጃ ቦታዎች የሚከተለው የመሬት ስፋት በስታንዳርድ ተቀምጧል፡፡**

### ሰንጠረዥ 13. የ ሚረጃ ቦታ ስታንዳርድ

| የህዝብ መገልገያ ቦታዎች | አስፈላጊው የወለል ስፋት | አስፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት |
|---|---|---|
| ማረጃ ቦታ | ---------- | 5000 — 7000 ካሜ |
| የእርድ ወጤቶች መሸጫ | 150 ካሜ | 200 ካሜ - 300 ካሜ |

2. **የህዝብ መፀዳጃ ቦታ**

**የህዝብ መፀዳጃ ቦታ ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

የህዝብ መፀዳጃ ቦታዎች በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች በሚከተሉት የህዝብ መሠብሰቢያ ቦታዎች ቢሆኑ ተመራጭ ይሆናል፡፡

- በህዝብ ትራንስፖርት መሳፈሪያ አካባቢ

- በገበያ
- በህዝብ መገናኛ ቦታ
- በህዝብ መዝናኛ ቦታ

ነገር ግን መፀዳጃ ቦታዎች ከመጠጥ ውሃ ምንጮች፣ ከወንወዝ መፋሰሻ መስመሮች የራቁ መሆን አለባቸው።

**የህዝብ ገላ መታጠቢዎች ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

- በመኖሪያ አካባቢ
- በስፖርት ማዘወተሪያ አካባቢዎች ቢሆኑ ይመረጣል

## ሰንጠረዥ14. የህዝብ ማዳጃ ቦታ ስታንዳርድ

| የህዝብ መገልገያ ቦታዎች | ሰፈላጊው የወለል ስፋት | አሰፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት |
|---|---|---|
| የህዝብ መፀዳጃ እና የህዝብ ገላ መታጠቢዎች | -------- | 300 ካሜ - 500 ካሜ |

**3.የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታ**

- የደረቅ የቆሻሻ ማስወገኛ ቦታ ስፋት በትንሹ 2000 ካ.ሜ መሆን አለበት ወይም በአንድ ሰው 0.6 ካ.ሜ ስሌት ተለክቶ መዘጋጀት አለበት።
- ከየቤቱ ከሚመነጩ ቆሻሻዎች መካከል የአፈሩን ለምነት የሚጎዱ ቆሻሻዎች ተለይተው ቀሪው በየቤቱ የቆሻሻ ጉድጓድ በማዘጋጀት እንዲቀበር ማድረግ ተገቢ ነው። የቆሻሻዎችንም ብስባሽ በማዳበሪያነት ለመጠቀምም ከግብርና ባለሞያዎች ጋር በመተባበር ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ይገባል። የአፈሩን ለምነት

የሚጎዱ ቆሻሻዎች ግን ምርታማነርን የሚጎዱ በመሆናቸው በጥናት በተለዩ ቦታ በሚዘጋጅ የቆሻሻ ማስወገኛ ቦታ በአጥር ከልሎ ማስወገድ ይገባል፡፡

- በቤት ለቤት የቆሻሻ ጉድጓድ በማዘጋጀት መቅበር የማይችሉ ቆሻሻ አመንጭዎች በቀበሌው አስተዳደር የቆሻሻ ሠራተኞች ለመሰብሰብ በሚያመች መልኩ በገንዳ ማጠራቀሚያ ተሰብስቦ ከሰባት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውሥጥ ወደ ዋናው ማጠራቀሚያ መወሰድ ይኖርበታል፡፡
- ገንዳዎቹ በግልጽ በሚታይ ቦታ መቀመጥ አለበቻው፡፡
- የገንዳው መጠን ቢበዛ 0.6 ሜ$^3$ መሆን አለበት
- አደገኛ ቆሻሻዎች ካሉ በጥንቃቄ ተለይተው በአግባቡ መያዝና እና መወገድ ይኖርባቸዋል

### 3. የማህበራዊ ደህንነት ቦታዎች

**የማህበራዊ ደህንነት ቦታዎች ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

የማህበራዊ ደህንነት ቦታዎች ለእድር፣ ለእቁብ እና ለመሳሰሉ ጉዳዮች የሚውሉ ቦታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የህዝብ መሰብሰቢያዎች ብዙን ጊዜ የዛፍ ጥላዎች በሚገኙባቸው ክፍት ቦታዎች የሚዘወተር ሲሆን ቀስበቀስ በቤት ውስጥ እየተዘወተረ መምጣቱ ስለማይቀር በገጠር ማዕከል በተለዩ ቦታዎች ላይ እንዲለሙ መደረግ አለበት፡፡

## ሰንጠረዠ 15. የ ማህበራዊ ደህንነ ት ስታንዳርድ

| የህዝብ መገልገያ ቦታዎች | ሰፊላጊው የወለል ስፋት | አስፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት |
|---|---|---|
| የማህበራዊ ደህንነት | ------- | 3000 — 5000 ካሜ |

## 2.2.5. ማዝናኛ፣ አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች

የመዝናኛ እና የአረንጓዴ ቦታዎች የግል ወይም የህዝብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ቦታዎች የህዝብ ባህላዊ ዕሴቶች ያሉባቸው ቦታዎች፣ ውብ ወይም የተለየ ተፈጥሮዎች ሚገኙባው

ቦታዎች፣ የቱሪስት መስህቦች፣ አረንጓዴ ቦታዎች፣ የመጫወጫ ቦታዎች፣ የሲኒማ እና ሌሎች ቦታዎችን ያጠቃልላል፡፡

### 1. የመዝናኛና ስፖርት ቦታዎች

**የስፖርት ቦታዎች ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

- በቦታ ላይ ያለቸው ስርጭት እኩል ሆኖ ለመኖሪያ አካባቢዎች በተመጣጣኝ ርቀት ላይ መሆን አለባቸው
- የስፖርትና መዝናኛ ስፍራዎች የተዳፋትነት መጠናቸው ዝቅተኛ (1-10%) ሆነው ከረግረግማ ቦታዎች የፀዱ ቢሆኑ ይመረጣል

## ሰንጠረዥ16. የ ስፖርት ቦታዎች ስታንዳርድ

| ለስፖርት አገልግሎት መስጫ ቦታዎች | የሜዳው ስፋት | አሰፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት | ተስማሚ የሳት ምርጫ |
|---|---|---|---|
| እግር ኳስ | 90ሜ*45 ሜ= 4050 ካሜ | 2 ሄክታር | በፓርኮች፣ በመዝናኛዎች አካባቢዎች፣ በክፍት ቦታዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ |
| አትሌቲክስ | 95ሜ*180ሜ = 17100 ካሜ | 2.5 ሄክታር | በፓርኮች፣ በመዝናኛዎች አካባቢዎች፣ በክፍት ቦታዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ |
| ቅርጫት ኳስ ሜዳ | 18ሜ*28ሜ= 504 ካሜ | 0.5 ሄክታር | በፓርኮች፣ በመዝናኛዎች አካባቢዎች፣ በቀበሌ አስተዳደር ውስጥ፣ በክፍት ቦታዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ |

| ለስፖርት አገልግሎት መስጫ ቦታዎች | የሜዳው ስፋት | አሰፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት | ተስማሚ የሳት ምርጫ |
|---|---|---|---|
| ሚ ብ ኳስ | 9ሜ*18ሜ= 162ካ ሜ | 0.5 ሄ ክ ታር | በ ፓርኮች፣ በ መዝናኛዎች አ ካባቢዎች፣ በቀበሌ አ ስተዳደር ውስ ጥ፣ በ ክፍት ቦ ታዎች በትምህ ር ት ቤቶች፣ ሌሎች ተቋማት ውስ ጥ |
| የ እ ጅ ኳስ | 1925ካ ሜ | 1 ሄ ክ ታር | በ ፓርኮች፣ በ መዝናኛዎች አ ካባቢዎች፣ በ ክፍት ቦ ታዎች በትምህ ር ት ቤቶች ፣ ሌሎች |
| | | | ተቋማት ውስ ጥ |
| የ ህ ጻ ና ት መጫወቻ ሜዳ | 200ካ ሜ- 300 ካ ሜ | 0.2 ሄ ክ ታር | በ ክፍት ቦ ታዎች በትምህ ር ት ቤቶች ፣ ሌሎች ተቋማት ውስ ጥ |
| የ ህ ጻ ና ትና ወጣቶች ማዕ ከ ል | 1000 – 2000 ካ ሜ | 0.5 ሄ ክ ታር | በ ፓርኮች፣ በ መዝናኛዎች አ ካባቢዎች፣ በ ክፍት ቦ ታዎች |
| የ ውሃ መዋኛ ገ ን ዳዎች | 25*13 | 425 ካ ሜ | በ ወን ዞ ች እ ና በ ሃ ይቅ ዳር ቻ በ ፓርኮች፣ በ መዝናኛዎች አ ካባቢዎች፣ |

*ምንጭ፡ ፌዴራል ደረጃዎች ኤጀንሲ*

## 1. አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች

### የመዝናኛ አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች ተስማሚ የሳይት ምርጫ

- በማዕከሉ ውስጥ በቦታ ላይ ያላቸው ስርጭት እኩል ሆኖ ለመኖሪያ አካባቢዎች በተመጣጣኝ ርቀት ላይ መሆን አለባቸው
- የመዝናኛ እና ክፍት ቦታዎች የህዝብ መገናኛ ቦታዎች ሊሆኑ ስለሚችሉ የተዳፋትነት መጠናቸው ዝቅተኛ (1-10%) ሚሆን አለበት
- ጥብቅ የአረንጓዴ ቦታዎች በተራራማ እና በወንዞች ዳርቻዎች አካባቢ ቢሆን ይመረጣል ነገር ግን የውበት ሥፍራዎች እንደአስፈላጊነቱ በአመቺ ቦታ ማድረግ ይቻላል

**የአረንጓዴ ልማት ዓይነቶች**

- ፓርኮች
- የስፖርት ሜዳዎች
- የማገድ አካፋይ፣ ዳርቻ እና አደባባዮች
- የፕላዛ እና የክብረበዓል ቦታዎች
- የወንዝ እና የሐይቅ ዳርቻ ቦታዎች
- የተፋሰስ ቦታዎች
- የገጠር የልማት ማዕከላት የግብርና ልማት ቦታዎች
- የገጠር ልማት ማዕከላት ዙሪያ ደን ልማት ቦታዎች
- የግለሰብ ግቢ እና አካባቢው
- የተቋማት ግቢ እና አካባቢው
- የዕምነት ተቋማት ግቢ እና አካባቢው
- በሰፈር ውስጥ የሚገኙ ክፍት ቦታዎች
- የዘላቂ ማረፊያ ቦታዎች
- የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎች
- የህንፃ ግድግዳዎች እና ጣሪያዎች
- ረግረግማቦታዎች

**አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች ስታንዳርድ**

## ሰንጠረዥ17. የአረንጓዴእና ክፍት ቦታዎች ስታንዳርድ

| አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች | አስፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| የአረንጓዴ እና ክፍት ቦታዎች | የገጠር ማዕከሉ የጥንስስ ከተማ የፕላን ወሰን 30% |
| የህዝብ መንግስታዊ እና ባህላዊ መሠብሰቢያ ቦታዎች | 20000 ካ.ሜ |
| የህዝብ ሁለገብ አዳራሽ | 2000 — 2500 ካ.ሜ |

### 2.2.6. ለአስተዳደር አገልግሎት

**የአስተዳደር አገልግሎት ቦታዎች ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

- በሁሉም አቅጣጫ
- በመጋቢ መንገድ ዳርቻዎች
- ከፖስታ ቤት እና ንኡስ ፖሊስ ጣቢያ ማዕከላት በስተቀር ሌሎች በንግድ ማዕከላት ውስጥ መሆን የለባቸውም
- ፖስታ ቤት እና ንኡስ ፖሊስ ጣቢያ በገበያ እና በመኖሪያ አካባቢ መሆን አለባቸው፡፡

## ሰንጠረዥ 18. የአስተዳደር አገልግሎት ቦታዎች ስታንዳርድ

| **የአስተዳደር አገልግሎት መስጫ ቦታዎች** | **አስፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት** |
|---|---|
| የቀበሌ አስተዳደር | 1000 — 3000 ካሜ |
| ንኡስ ፖሊስ ጣቢያ | 200 — 500 ካሜ |
| የማህበራዊ ፍርድ ቤት | 200 — 500 ካሜ |
| መንግስታዊ ተቋማት | 500 — 1000 ካሜ |
| መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት | 500 — 1000 ካሜ |
| ፖስታ ቤት | 50 — 100 ካሜ |
| ማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ጣቢያ | 100 — 300 ካሜ |
| የህብረት ሥራ ምህበራት | 2000 - 3000 |

### 2.2.7. የአነስተኛ ኢንዱስትሪ

**የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ተስማሚ የሳይት ምርጫ**

- በካይ እንዱስትሪዎች ከንፋስ አቅጣጫ በተቃራኒ አካባቢዎች መልማት አለባቸው
- በካይ እንዱስትሪዎች ከመኖሪያ፣ ከትምህርት እና ከጤና ተቋማት የራቁ መሆን አለባቸው
- የገጠር ማዕከሏን ውበት ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ መልማት አለባቸው

## ሰንጠረዥ 19. የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ቦታዎች ስታንዳርድ

| የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ቦታዎች | በሽድ ለሚገነቡ አስፈላጊው የቁራሽ መሬት ስፋት | አስፈላጊው የቁራሽ ስፋት (PA) በክላስተር | አስፈላጊው የቁራሽ ስፋት (PA) በነጠላ |
|---|---|---|---|
| **የግብርና ምርት ውጤቶች ማቀናበሪያ** | | | |
| የወተት እና የወተት ምርት ውጤቶች ማቀነባበሪያ | --------- | 10000- 20000 | 1000 — 2000 ካሜ |
| የቡና ቦርድ( የቡና እጥበትና የገለባ ማጣሪያ ወፍጮ) | --------- | 10000 - 20000 | 1000 — 2000 ካሜ |
| የቡና መፍጫ እና ማሽጊያዎች | 200 ካ.ሜ | 10000 — 20000 ካሜ | 1000 — 2000 ካሜ |
| የምግብ ዘይት | 150 ካ.ሜ | 3000 — 5000 ካ.ሜ | 300 — 600 ካ.ሜ |
| የምግብ ወፍጮ ቤት | 150 ካ.ሜ | 5000 — 10000 (ለ5 እና ከዚያ በላይ) | 200 — 300 ካሜ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዳቦ ቤት | 150 ካ.ሜ | ------ | 150 — 300 ካሜ |
| የባልትና ውጤቶች ምርት | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 - 2000 | 100 — 300 ካሜ |
| **ሌሎች አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች** | | 3000 — 120000 ካሜ ካሜ (በሚቀርበው የኢንዱስትሪው መንደር ቅርጽ መሠረት) | 1000 — 2000 ካሜ |
| **የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ወይም እደ-ጥበባት** | | | |
| የእንጨት ሥራ | 50 - 80 ካ.ሜ | 3000 — 10 000 | 200 — 300 ካሜ |
| የቀርከሃ ሥራ | 50 - 80 ካ.ሜ | | 100 — 200 ካ ሜ |
| የልብስ ስፌት | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 2000 ካ ሜ | 50 — 150 ካሜ |
| ባህላዊ ሽመና | 80-120 ካ.ሜ | 1000 — 2000 ካ ሜ | 50 — 150 ካ ሜ |
| ቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 2000 ካ.ሜ | 100 — 200 ካ.ሜ |
| የዘንባባ ስራ | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 2000 ካ.ሜ | 100 — 200 ካ.ሜ |
| የስጋጃ ሥራ | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 2000 ካ.ሜ | 80 — 150 ካ ሜ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የሹራብ ሥራ | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 2000 ካ.ሜ | 80 — 150 ካ.ሜ |
| የጥልፍ ስራ | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 2000 ካ.ሜ | 80 — 150 ካ.ሜ |
| ባህላዊ ብረታብረት ስራ | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 2000 ካ ሜ | 80 — 100 ካ ሜ |
| የሸክላ ሥራ | 100-150 ካ.ሜ | 1000 — 5000 ካ ሜ | 200 ካ ሜ |
| የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 5000 ካ ሜ | 80 — 150 ካ.ሜ |
| የዱቄት እና ፈሳሽ ሳሙና | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 5000 ካ ሜ | 100 — 150 ካሜ |
| ወርቅ ቤት | 50 - 80 ካ.ሜ | 1000 — 5000 ካ ሜ | 50 — 100 ካሜ |
| ጋራዥ | ------ | ------ | 500 — 1000 ካሜ |
| ጎሚስታ | ------ | ------ | 100 — 200 ካሜ |
| ነዳጅ ማደያ | ------- | ------ | 1000 — 2000 ካሜ |
| ብሎኬት ማምረቻ | ------ | ------ | 1000 ካ.ሜ |

# 3. የመንገድና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች መረብ ስታንዳርድ

## 3.1. መንገድ ስታንዳርድ

### 3.1.1. የ መን ገ ድ ሚ ብ ቅረ ጽ

የገጠር የልማት ማዕከላት የመንገድ መረብ ፕላን ሲዘጋጅ ትኩረት ሊሰጥ የሚገቡ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. የመኪና እና የሰው ትራፊክ ፍሰት መጠን

ለ. የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ

ሐ. የተፈጥሮ የመሬት አቀማመጥ ሁኔታ

መ. የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ጉዳዮች


ሠ. የግንባታ ወጪ መጠን

**1. የመንገድ መረብ ዓይነቶች**


የገጠር ማዕከሏን ጠፈጥሮአዊ የመሬተት አቀማመጥ፣ የአዬር ጠባይ፣ እና ነባራዊውን የትራንስፖርት መስመሮችን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት በተለያዩ የመንገድ መረቦች አይነቶች ፕላን ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

**ሀ. የራዲያል የመንገድ መረብ** ፦ የዚህ ዓይነቱ የመንገድ መረብ ከመሃል ከአንድ ነጥብ በቀጥታ ወደ ዳር በተለያዩ አቅጣጫዎች በሚዘረጉ መንገዶች የማእከሏን የመንገድ መረብ መቅረፅ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የመንገድ መረብ በሁለት አይነት መንገድ ሊዘረጋ ይችላል፡፡


1. በሸረሪት ድር የሚመሰል





2. የክቦች ንብርብር የሚመስል




**ለ. የአራት ማዕዘን መንገድ መረብ ፦** የዚህ አይነቱ የመንገድ መረብ በአራት ማዕዘን ቅርፅ የሚዘጋጅ ነው





**ሐ. ቅይጥ መንገድ መረብ ( የራዲያል እና የአራት ማዕዘን )** ፦ ከላይ በክብ እና በአራት ማዕዘን ቅርጽ ተቀይጦ የሚዘጋጅ የመንገድ መረብ ነው።




**መ. ቅርፅ አልባ የመንገድ ሚብ ቅርፅ** ፦ ምንም ትርጉም ያለው ቅርፅ ሳይኖረው የሚዘጋጅ የመንገድ መረብ ነው።

***ሠ. ሌሎች የመንገድ መረብ ቅርፆች*** ፦ በኮከብ ቅርፅ ወይም አንድ መንገድ ብቻ ያለው የመንገድ ቅርጽ፡፡



### 3.1.2. የ ማን ገ ድ ስፋት ስ ታን ዳርድ

1. በሁለት መንገዶች መካከል ያለው የመንገድ ሥፋት ስታንዳርድ

## ሰ ን ጠረ ዥ20. በ ሁለ ት ማን ገ ዶች ማካ ከል ያ ለ ውስፋት ስ ታን ዳር ድ

| ተ.ቁ | የመንገድ አይነት | የስፋት ስታንዳርድ |
|---|---|---|
| 1 | የፍጥነት መንገድ | ጥንስስ ከተማዋን አቋርጦ የሚያልፍ ካለ አንድ መንገድ |
| 2 | አንደኛ መንገድ | 1 ኪ.ሜ — 2 ኪ.ሜ |
| 3 | ሁለተኛ መንገድ | 0.5 ኪ.ሜ — 1 ኪ.ሜ |
| 4 | የሶስተኛ መንገድ | 0.25 ኪ.ሜ — 0.5 ኪ.ሜ |
| | የሰፈር መንገድ | 0.03 ኪ.ሜ — 0.25 ኪ.ሜ |

2. የመንገዶች ስፋት

## ሰንጠረዥ21. የ መንገዶች ስፋት ስታንዳርድ

| ተ.ቁ | የመንገድ አይነት | የስፋት ስታንዳርድ |
|---|---|---|
| 1 | የፍጥነት መንገድ | አቋርጦ የሚያልፍ መንገድ ካለ መለካት |
| 2 | አንደኛ መንገድ | 30 ሜ - 40ሜ |
| 3 | ሁለተኛ መንገድ | 20 ሜ - 30 ሜ |
| 4 | የሶስተኛ መንገድ | 15 ሜ - 16.5 ሜ |
| 5 | የሰፈር መንገድ | 6ሜ - 12 ሜ |

3. መንገዶች ሲገነቡ የመስመሮች ቁጥር እና ስፋት

## ሰንጠረዥ22. መንገዶች ሲገነቡ የ መስመሮች ቁጥር እና ስፋት ስታንዳርድ

| ተ.ቁ | የመንገድ አይነት | የተቃራኒ መስመሮች ቁጥር ብዛት Carriage way | ጠቅላላ የውስጥ መስመሮች ቁጥር(lanes) | የአንዱ የውስጥ መስመር ስፋት ስታንዳርድ በሜትር | የእግረኛ መንገድ ስፋት በሜትር | የአካፋይ መንገድ ስፋት በሜትር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የፍጥነት መንገድ | 2 - 4 | 6 | 3-4 | ….. | …… |
| 2 | አንደኛ መንገድ | 2 | 4 | 3- 3.5 | 3.75- 4.50 | 3 |
| 3 | ሁለተኛ መንገድ | 2 | 2 | 3 | 2.75- 3.5 | 1.5 -2 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የሶስተኛ መንገድ | 1 | 2 | 3 | 2- 3.5 | -- |
| 5 | የሰፈር መንገድ | 1 | 1 | 4 | 0 | -- |

4. የትንንሽ እና ማካከለኛ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ማናኸሪያ የቁራሽ ሜዳ ስፋት ማጠን፡

   10 ሚኒባሶችን በቀን የሚያስተናግድ ከሆነ የቁራሽ ሜዳ ስፋት ማጠን 1.5 ሄክታር መሆን አለበት

### 3.1.3. የመንገድ መገናኛዎች

በገጠር የልማት ማዕከላት በስኬች ፕላን ዝግጅት የመንገድ መገናኛዎች በሚከተሉት መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ

- በእንግሊዘኛው ፊደል በT ቅርፅ መንገዶችን ማገናኘት ( T Junction) -
- እርስ በርስ በሚተላለፉ (cross Junction) - በአራት አቅጣጫ በሚመጡ መንገዶች በአንድ አደባባይ ላይ የሚተላለፉ መንገዶች፡፡

**የመንገድ መገናኛዎች ቦታ ምርጫ**

- የመንገድ መገናኛዎች ቦታዎች በጠመዝማዛ እና የታዳፋት መጠናቸው ከ6% በላይ በሆኑባቸው ቦታዎች ላይ መሆን የለባቸውም፡፡
- የመንገድ መገናኛዎች ቦታዎች የትራፊክ መጨናነቅ በሚፈጠርበት ሁኔታ የተቀራረቡ መሆን የለባቸውም

### 3.1.4. የመንገዶች ተሚራጭያ ተዳፋትነት ማጠን

የመንገድ መረቦችን በተመጣጣኝ የተዳፋትነት መጠን እንዲለሙ ማድረግ መንገዶች ቀና እና አመቺ እንዲሆኑ ከማድረጉም በላይ ለማልማት ወጪ ቆጣቢ እና አዋጪ እንዲሆን ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም የመንገድ መረቦችን በተመጣጣኝ የተዳፋትነት መጠን

እንዲለሙ ፕላን ማድረግ ለማዕከሏ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ትስስርን በማሳለጥ ወደፊት ሁለንተናዊ ዕድገት ያፋጥናል፡፡

የመንገዶች መረብን በተፈላጊው የተዳፋትነት መጠን ለመቅረፅ ጠቃሚ ማስታወሻዎች

- የመንገዶች ተዳፋትነት ለእይታ፣ ለምቾት፣ ለፍሳሽ መስመሮች እና ለውበት የሚያመች መሆን አለበት
- የመንገዶች መረቦች ከፍተኛ የጎርፍ ማጥለቅለቅ በማይፈጠርበት ሁኔታ አግድም በሚዘረጉ መንገዶች መቀረፅ አለበት

**የመንገዶች የተዳፋትነት መጠን**

## ሰንጠረዥ 23. የምንገዶች የተዳፋትነት ማጠን

| ተ.ቁ | የመንገዶች ዓይነት | የተዳፋትነት መጠን በመንገዱ ላይ |
|---|---|---|
| 1 | የተሽከርካሪ መንገድ | 1 - 12 % |
| | | 1 - 6 % (መጠማ ዘዣ መንገድ) |
| 2 | እግረኛ | 1- 35% |
| 3. | ባቡር | 1 — 4% |

### 3.1.5. ብስክሌት እና የእግረኛ ማንገድ ሚብ

የገጠር የልማት ማዕከላት የውስጥ ለውስጥ እና ከአንዱ ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ የሚደረገው እንቅስቃሴ በአመዛኙ በእግር እና በብስክሌት በመሆኑ ለነዚህ የመገናኛ ዘዴ ትኩረት ሰጥቶ በቂ የመንገድ መስመር እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ መንገዶችም በዋና መንገዶች ላይ የተለያየ መስመር ሊኖራቸው ይገባል፡፡

**ብስክሌት**

1. የመስመሩ ዝቅተኛው ስፋት በሁለቱም አቅጣጫ 3 ሜ

2. የብስክሌት መስመር የተዳፋትነት መጠን 3 — 5 %

**የእግረኛ መንገድ**

- ሁሉም መንገዶች በግራና በቀኝ በቂ የእግረኛ መንገድ ሊኖቸው ይገባል
- የእግረኛ መንገዶች ከዋናው መንገድ ከ15 — 20 ሳ.ሜ ከፍታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- የእግረኛ መንገዶች የፍሳሽ መስመራቸው ቢያንስ በ2.5 የተዳፋትነት መጠን መሠራት አለባቸው፡፡
- ከመንገድ ውጭ የሚታቀዱ የእግረኛ መስመሮች የተዳፋትነት መጠን ከ 10 — 35 %
- እያንዳንዱ የእግረኛ መንገድ ቢያንስ በአንዴ ወደ 20 ሰው የሚሸከም መሆን ስላለበት ስፋቱ በ6 ሜትር መሠራት አለበት ፡፡

**የእግረኛ መንገድ ስፋት**

- ወደ ንግድ ሱቆች የሚወስድ የእግረኛ መንገድ 3 ሜ
- ወደ ገበያ የሚወስድ የውስጥ ለውስጥ የእግረኛ መንገድ 4 ሜ
- ወደ ሁሉም አገልግሎቶች የሚወስድ የእግረኛ መንገድ 2 ሜ

**3.1.6.የ ማኪና ማቆሚያ**


በሃይማኖታዊ በዓላት፣ በንግድ፣ በሰርግ፣ በለቅሶ አና በሌሎችም ምክንያቶች ወደ ገጠር የልማት ማዕከላት የሚንቀሳቀሱ የንግድ እና የቤት መኪናዎች ማቆያ የሚፈልጉ በመሆናቸው በማዕከሉ አማካይ ቦታ ላይ እና በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ላይ የፓርኪንግ ቦታ ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

## ሰንጠረዥ24. የፓርኪንግ ቦታ ስታንዳርድ

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀሙ አይነት | ተፈላጊው የመሬት መጠን ተዛማጅነት |
|---|---|---|
| 1. | በገበያ እና በንግድ ማዕከላት | በአንድ መኪና 100 ካ.ሜ$^2$ |
| 2. | በአገልግሎት እና በአስተዳደር ቦታዎች | በአንድ መኪና 250 ካ.ሜ$^2$ |
| 3. | በመኖሪያ አካባቢ | በየቤቱ |
| 4. | መዝናኛ | በአንድ መኪና 250 ካ.ሜ$^2$ |

### 3.2.የአገልግሎቶች  ስታንዳርድ

**የአገልግሎት ማስመር ዝርጋታ ከዋነ ውሜገድ በማሳት ያለውቅደምተከተል**





**<u>መግለጫ</u>**

**E= የሃይል ማስመር  F= የነዳጅ ማስመር  D= የጎርፍ ፍሳሽ ማስመር T= የቴሌፎን ማስመር  $W_I$= የማስኖ ውሃ ማስመር  S= የእጣቢ ፍሳሽ ማስመር  W= የማጠጥ ውሃ ማስመር  $T_S$= የትራፊክ ምልክት**

# በመንገዶች ላይ የአገልግሎት ማስመሮች ስፋት ስታንዳርድ

## ምስል 1. ባለ 8 ሜትር መንገድ

8 ሜትር





## ሰንጠረዥ25. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ8 ሜትር ስፋት

| የአገልግሎቶች ስታንዳርድ በ8 ሜትር | | |
|---|---|---|
| የአገልግሎቶች ዓይነት | የትቦ ስፋት በሚሜ | የማስመሩ ስፋት በሚሜ |
| የውሃ ማስመር | 600 | 1300 |
| የፍሳሽ ማስመር ስፋት | 900 | 1800 |

| | | |
|---|---|---|
| **የጎርፍ ፍሳሽ ማስመር ስፋት** | **900** | **1750** |
| **የሀይል ማስመር ስፋት** | **------** | **800** |
| **የቴሌ ማስመር** | **-------** | **800** |

ምስል 2. ባለ 16.50 ሜትር መንገድ





## ሰንጠረዥ26. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ16.50 ሜስፋት

| **የአገልግሎቶች ስታንዳርድ በ 16.50 ሜትር** | | |
|---|---|---|
| **የአገልግሎቶች ዓይነት** | **የትቦ ስፋት በሚሜ** | **የማስመሩ ስፋት በሚሜ** |
| **የውሃ ማስመር** | **600** | **1300** |
| **የፍሳሽ ማስመር ስፋት** | **900** | **1750** |


| | | |
|---|---|---|
| **የ ጎርፍ ፍሳሽ ማስመር ስፋት** | **900** | **1800** |
| **የ ሀይል ማስመር ስፋት** | **------** | **800** |
| **የ ቴሌ ማስመር** | **------** | **800** |
| **የ ትራፊክ ምልክት** | **-------** | **1000** |

## ምስል 3. ባለ 20 ሜትር መንገድ




## ሰንጠረዥ27. የ አገልግሎት ስታንዳርድ በ20 ሜትር

## ምስል 4. ባለ 25 ሜትር መንገድ





| የአገልግሎቶች ስታንዳርድ በ20 ሜትር | | |
|---|---|---|
| **የአገልግሎቶች ዓይነት** | **የትቦ ስፋት በሚሜ** | **የማስመር ስፋት በሚሜ** |
| **የውሃ ማስመር** | **700** | **1300** |
| **የፍሳሽ ማስመር ስፋት** | **900** | **1750** |
| **የጎርፍ ፍሳሽ ማስመር ስፋት** | **900** | **1800** |
| **የሀይል ማስመር ስፋት** | **------** | **1080** |
| **የቴሌ ማስመር** | **------** | **1080** |
| **የትራፊክ ምልክት** | **-------** | **1000** |

## ሰንጠረዥ28. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ25 ሜትር

| ስታንዳርድ በ25 ሜትር | | |
|---|---|---|
| የአገልግሎቶች ዓይነት | የትቦ ስፋት በሚሜ | የማስመሩ ስፋት በሚሜ |
| የውሃ ማስመር | 700 | 1300 |
| የፍሳሽ ማስመር ስፋት | 900 | 1750 |
| የጎርፍ ፍሳሽ ማስመር ስፋት | 900 | 1800 |
| የሀይል ማስመር ስፋት | ------ | 1150 |
| የቴሌ ማስመር | ------ | 1150 |
| የትራፊክ ምልክት | ------- | 1000 |

## ምስል 5. ባለ 30 ሜትር መንገድ




## ሰንጠረዥ29. የአገልግሎት ስታንዳርድ በ30 ሜትር

| ስታንዳርድ በ 30 ሜትር | | |
|---|---|---|
| **የአገልግሎቶች ዓይነት** | **የትቦ ስፋት በሚሜ** | **የማስመሩ ስፋት በሚሜ** |
| **የውሃ ማስመር** | **800** | **1300** |
| **የፍሳሽ ማስመር ስፋት** | **900** | **1750** |
| **የጎርፍ ፍሳሽ ማስመር ስፋት** | **900** | **1800** |
| **የሀይል ማስመር ስፋት** | **------** | **1150** |
| **የቴሌ ማስመር** | **------** | **1150** |
| **የትራፊክ ምልክት** | **-------** | **1000** |


የመንገድ የቀለማት ስታንዳርድ

## ሰንጠረዥ 30. የመንገድ ቀለማት ስታንዳርድ

| No | የመንገድ ዓይነት | የቀለማት ኮድ | | Color of Gradient of Streets for Land use Maps | የቀለማት ውፍረት | የማዕከል ማስመሩ ቀለምእና ቅርፅ (line weight (0.30) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አንደኛ መንገድ | ቀይ | | ዋና መንገድ | 0.60 Block | |
| 2 | ሁለተኛ መንገድ | ሰማያዊ | | የዋና መንገድ መጋቢ | 0.40 Block | |
| 3 | ሶስተኛ መንገድ | ደማቅ ብርሃንማ | | የሁለተኛ መጋቢ መንገድ | 0.20 Block | |
| 4 | የሰፈር መንገድ | | | | 0.10 Block | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የውስጥ ለውስጥ መንገድ | | |
| | | | | | | |

ምሳሌ



የአገልግሎቶች የቀለማት ስታንዳርድ

## ሰንጠረዥ 31. የአገልግሎት ቀለማት ስታንዳርድ

| No | የአገልግሎት አይነቶች | የአገልግሎቶች ቀለማት እና በአገልግሎቶች መካከል አካፋይ ቀለም | | በአገልግሎቶች እና በመንገድ መካከል አካፋይ ቀለም | የነጠላ መስመር ቀለማት እና ቅርፅ (line weight 0.60) |
|---|---|---|---|---|---|
| | የመጠጥ ውሃ መስመር | ሰማያዊ | | | |
| 2 | የፍሳሽ መስመር | ቢጫ | | | |
| 3 | የጎርፍ ፍሳሽ መስመር | አረንጓዴ | | | |
| | | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የ ሀይል ማስሞር ስፋት | ቀይ | | | |
| 5 | የ ቴሌ ማስሞር | ብርትኳንማ | | | |
| 6 | መንገ ድና አረንጓዴ | ደናቅ አረነ ረጓዴ | | | |

በየደረጃውያለውየቧንቧ ማስመሮች የቀለማት ኮድ

| No | የቧንቧ ማስመሮች ዓይነት | Color of Gradient of utility for utilities Network Maps | | Color of Gradient of street and water supply for water supply network Maps | Shape and color designated by single |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከማጠራቀሚያው ጋን የሚወጣ ዋናው የቧንቧ ማስመር | ወይን ጠጅ | | ዋና መንገድ | (line weight 0.60) |
| 2 | የመጀመሪያ ቅርንጫፍ | ፈዛዛ ሰማያዊ | | የዋና መንገድ መጋቢ | (line weight 0.40) |
| 3 | ሁለተኛ ቅርንጫፍ | ደማቅ ሰማያዊ | | የሁለተኛ መጋቢ መንገድ | (line weight 0.30) |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ሶስተኛ ቅርንጫፍ | ጥቁር ሰማያዊ | | የውስጥ ለውስጥ መንገድ | (line weight 0.20) |

## የፍሳሽ ማስመር

| No | **የፍሳሽ ማስመር** ዓይነት | Color of Gradient for sewerage line Network Maps | | Color of Gradient of street and sewerage line for sewerage line network Maps | Shape and color by single |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዋና ውየ ፍሳሽ ማስመር | ፈዛዛ ብጫ | | ዋና መንገድ | (line weight 0.60) |
| 2 | የመጋቢያ ቅርንጫፍ | ብጫ | | የዋና መንገድ መጋቢ | (line weight 0.40) |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 3 | ሁለተኛ ቅርንጫፍ | ብጫ ት ያለው አረንጓዴ | | የሁለተኛ መጋቢ መንገድ | (line weight 0.30) |
| 4 | ሶስተኛ ቅርንጫፍ | ቅጠልማ | | የውስጥ ለውስጥ መንገድ | (line weight 0.20) |

**የጎርፍ ፍሳሽ ማስመር ስፋት**

| No | storm pipe line type | Color of Gradient for storm water line network Maps | | Color of Gradient of streets and storm water line for storm water line network Maps | Shape and color by single |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዋናውየ ፍሳሽ ማስመር | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | ፈዛዛ<br>ብርሃንማ<br>አረንጓዴ | | ዋና መንገድ | (line weight 0.60) |
| 2 | የመጀመሪያ ቅርንጫፍ | ደማቅ<br>ብርሃንማ<br>አረንጓዴ | | የዋና መንገድ መጋቢ | (line weight 0.40) |
| 3 | ሁለተኛ ቅርንጫፍ | አረንጓዴ | | የሁለተኛ መጋቢ መንገድ | (line weight 0.30) |
| 4 | ሶስተኛ ቅርንጫፍ | ደማቅ<br>አረንጓዴ | | የውስጥ ለውስጥ መንገድ | (line weight 0.20) |

**የ ሀይል ማስመር ስፋት**

| No | የ ሃ ይል ማስ መር ዓይነ ት | Color of Gradient for power supply network Maps | | Color of Gradient of streets and power supply line for power supply network Maps | Shape and color by single |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከንኡስ ስቴሽን የሚወጣው የ ሃ ይል ማስ መር | Light Coral | | ዋና መንገድ<br>ከፍተኛ ሃይል | (line weight 0.60) |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዋና መንገድ<br>መካከለኛ ሃይል | |
| | | | | ዋና መንገድ<br>ዝቅተኛ ሃይል | |
| 2 | አንደኛ የሃይል ማስሚር | ደማቅ ቀይ | | የዋና መንገድ መጋቢ<br>ከፍተኛ ሃይል | (line weight 0.40) |
| | | | | የዋና መንገድ መጋቢ<br>መካከለኛ ሃይል | |
| | | | | የዋና መንገድ መጋቢ<br>ዝቅተኛ ሃይል | |
| | | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ሁለተኛ የሃይል ማስመር | ቀይ | | የሁለተኛ መጋቢ መንገድ<br>መካከለኛ ሃይል | (line weight 0.30) |
| | | | | የሁለተኛ መጋቢ መንገድ<br>ዝቅተኛ ሃይል | |
| 4 | ሶስተኛ የሃይል ማስመር | ደማቅ ቀይ | | የውስጥ ለውስጥ መንገድ<br>መካከለኛ ሃይል | (line weight 0.20) |
| | | | | የውስጥ ለውስጥ መንገድ<br>ዝቅተኛ ሃይል | |

**የቴሌ ማስመር**

| No | **የቴሌ ማስመር ዓይነቶች** | Color of Gradient for power supply network Maps | Color of Gradient of streets and power supply line for power supply | Shape and color by single |
|---|---|---|---|---|

| | | | | network Maps | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **ዋና ውየ ቴሌ ማክሮ** | ብርትኳንማ | | ዋና መንገድ | (line weight 0.60) |
| 2 | አንደኛ የ ቴሌ ማክሮ | ደማቅ ብርትኳንማ | | የዋና መንገድ መጋቢ | (line weight 0.40) |
| 3 | ሁለጠኛ የ ቴሌ ማክሮ | ቡኒ | | የሁለተኛ መጋቢ መንገድ | (line weight 0.30) |
| | | | | የውስጥ ለውስጥ መንገድ | (line weight 0.20) |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ሦስተኛ የቴሌ ማስሚር | ደማቅ ቡኒ | | | |

## 4. የወረቀት፣ የስኬል እና የብሎክ ስታንዳርዶች

### 4.1. የስኬች ፕላን የወረቀት እና ማስፈርት የተማከተ

**ሀ. የወረቀት መጠን**

- ስታንዳርድ የወረቀት መጠን A2፣ A1፣ A0
- ፕላኑ በበቂ የዳርቻ መግለጫዎች መሰራት አለበት
  - ➢ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ
  - ➢ ዋናዋና መግለጫ ( legend)

**ለ. መስፈርት**

- ስኬች ፕላን ከ 1:5000 — 1፡ 2000 በሚደርስ ስኬል ይዘጋጃል

#### ሰንጠረዥ32. የስኬች ፕላን ማስፈርት ስታንዳርድ

| የፕላኑ ወሰን የመሬት መጠን | መስፈርት |
|---|---|
| ከ 20 — 50 ሄክታር | 1፡ 2000 |
| ከ50 — 100 ሄክታር | 1፡ 3000 - 1፡ 2500 |
| ከ100 — 250 ሄክታር | 1፡ 5000 |

### 4.2. የ ብሎክ ማጠን

**የብሎክ መጠን**

- ርዝመት 80ሜ - 170ሜ
- ስፋት 40 ሜ - 80 ሜ

## ማጣቀሻዎች

ከልቤኮሚ (2007 ዓ.ም). የኢትዮጰያ የብሔራዊ የከተማ አረንጓዴ መሠረተ ልማት ስታንዳርድ፡

ከልቤሚ (2009 ዓ.ም). የስኬች ፕላን ማዘጋጃ እና ትግበራ ሞዴል ማንዋል ቁጥር 24/2008

ከልኮሚ (2005) - ከከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር አንፃር ዘላቂ የከተማ ግብርና ማስፋፊያ ጥናት

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት (2008). በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የቦታ ሽንሳኖ ስታንዳርድ መመሪያ ቁጥር 9/ 2009

ትምህርት ሚኒስቴር (2001). የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስታንዳርድ

ትምህርት ሚኒስቴር (2001). የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ደረጃ መለኪያ ስታንዳርድ

ትምህርት ሚኒስቴር (2001). የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ስታንዳርድ

ማስኤ (2005 ዓ.ም). የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የ2005 የህዝብ ቁጥር ትንበያ መረጃ

The Republic of Uganda(2011). National Physical Planning Standards and Guid Line

MUDCo(2012). Revised Standards For Structure Plan Preparation And Implementation

ከልቤኮሚ(2003). ክፍለኢኮኖሚ የአምስት አመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ

ከልቤኮሚ (2006) የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ዝግጅት እና አፈፃፀም ስትራቴጂ

ከልቤሚ (2008). የስኬች ፕላን ማዘጋጃ እና ትግበራ ሞዴል ማንዋል ቁጥር 24/2008

CSA (2007) The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia.

CSA(2013). **Population Projection Of Ethiopia For All Regions At Wereda Level From 2014 – 2017**

**FIIDCA(2017). Utility Corridors Design Standard Within Streets Row.**

MUDHo (2016). Natonal Urban Development Spatial Plan.

**MUDH (2017). Street Design Standards for Urban Ethiopia**

NUPI(2004). **የከተማ ፕላን አዘገጃጀት አፈፃፀም ችግሮች እና የመብትሔ አቅጣጫዎች**

United Nations (1990) Human Development Report: Oxford University Press

United Nations (1991) . World Urbanization Prospects, New York

United Nations (2002) Press Release, POP/815, 21 March, p 1.